# የኢ.ማ.ማ.ተ ዕጩ ተማሪዎች ምዝገባ መስፈርቶች፣ ትዕዛዞችና መመሪያዎች

## ለመርሃ ግብሩ ለማመልከት የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች

- ኢትዮጵያዊ/ ፣ ያታ
- መርሃ ግብሩ/ትምህርቱ በሚጀምርበት ጊዜ ዕድሜው/ ከ26 ዓመት በላይ ያልሆነ
- በእንግሊዝኛ ቋንቋ ጥሩ የመናገርና የመፃፍ ችሎታ ያለው/
- ከፌዴራል ፖሊስ የወንጀል ሪከርድ እንደሌለው/ የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል

## የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

- በኤሌክትሪካል ኢንጂነሪንግ፣ በኤሌክትሮ ሜካኒካል ኢንጂነሪንግ፣ በኤሌክትሮኒክስ፣ በኮሙኒኬሽንና ኮምፒውተር BSc ዲግሪ ያለው/

## የስልጠና መርሃ ግብሩን ለመቀላቀል የሚያስፈልጉ መግቢያ ደረጃዎችና ቅድመ ሁኔታዎች

## የሚከተሉትን ደረጃዎች በስኬታማነት መጨረስ

## ደረጃ 1፡ የመለየት ሂደት

- በኢ.ማ.ማ.ተ. የሚዘጋጅ የጽሁፍ የመግቢያ ፈተናና ለቃለ መጠየቅ ለመጠራት የተቀመጠውን ዝቅተኛ ውጤት ማስመዝገብ ይጠበቅ ል፤
- የመግቢያ ፈተናውን ካለ በኋላ ቃለ መጠይቅ በኢ.ማ.ማ.ተ የቃለመጠይቅ ጉባኤ ለመርሃ ግብሩ ተቀባይነት ማግኘት ያስፈልጋል

## ደረጃ 2፡ የቅበላና ዋስትና ስምምነት መፈረም

ዕጩ ተማሪውና ዋሱ የቅበላ ስምምነቱን ከመፈረማቸው በፊት የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው፤

## ሰነዶች

- ከተማሩበት ዩኒቨርሲቲ የዲሲፕሊን ማረጋገጫ ደብዳቤ - ተማሪው በካምፓስ ቆይታው ምንም ዓይነት የስነ-ምግባር ችግር እንዳልነበረ የሚያሳይ
- መርሃ ግብሩ/ትምህርቱ ከጀመረ ቢያንስ ከስድስት ወር በኋላ የአገልግሎት ጊዜው የሚያበቃ የፀና የቀበሌ መታወቂያ
- ፓስፖርት ካለ
- ከሁለቱም የቤተሰብ ዋሶች ጋር ያለውን የጋብቻ ወይም የስጋ ዝምድና የሚያሳይ ማስረጃ
- ያላገባ ከሆነ ይህን የሚያሳይ ማስረጃ፣ ያገባ ከሆነ የባለቤቱ ፊርማና በአካል መቅረብ አስፈላጊ ነው
- ከፌዴራል ፖሊስ የወንጀል ሪከርድ እንደሌለው የሚያሳይ ማስረጃ

## ፈቃዶች

- የቅበላ እና የዋስትና ስምምነቶች በሚፈረምበት ወቅት የሚፈፀም "የቅድመ ትንበያ ግምገማ" ለመውሰድ የሚፈቅድ ስምምነት

**ዋሶች**

- ሁለት የቤተሰብ አባሎች
- በእጩ ተማሪውና በቤተሰብ ዋሶች መካከል ያለው ዝምድና ከሶስት ደረጃ የዘለለ መሆን የለበትም ማለትም (እናት፣ አባት፣ እህት፣ የእህት ባል፣ ወንድም፣ የወንድም ሚስት፣ ሴት አያት፣ ወንድ አያት፣ አክስት፣ አጎት፣ የአክስት ልጅ እና የአጎት ልጅ)

**ዋሱ የዋስትና ሰነዱን ከመፈረሙ በፊት የሚከተሉትን ሰነዶች ማቅረብ ይኖርበታል**

- የፀና እና የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ (ዋናው እና ኮፒ)
- ዋሱ ያገባ ከሆነ የጋብቻ የምስክር ወረቀት (ዋናው እና ኮፒ)፣ ዋሱ ያላገባ ከሆነ የቀበሌ መታወቂያውን ከሰጠው አካል እንዳላገባ የሚገልጽ ማስረጃ ማምጣት አለበት፡፡
- ዕጩ ተማሪው እና ዋሱ (ዋሶቹ) ያገቡ ከሆኑ የእጩ ተማሪው እና ዋሱ(ዋሶቹ) የትዳር አጋር በአካል ቀርበው የቅበላ/ዋስትና ስምምነቶቹን መፈረም አለባቸው
- ግለሰቡ ከሚሰራበት መ/ቤት የዋሱን ወርሃዊ ደመወዝ የሚገልጽ (ደመወዙ ከ5,000 ብር ያላነሰ መሆን አለበት)፣ ቋሚ ሠራተኛ መሆኑን፣ በተጨማሪም ሠራተኛው መ/ቤቱን ቢለቅ መ/ቤቱ አስቀድሞ የሚያሳውቅ መሆኑ በደብዳቤው ላይ መጠቀስ አለበት
- የንብረት ባለቤትነት ማረጋገጫ፡ የቤት ካርታ ወይም የመኪና ሊብሬ
- የፖስታ ሳጥን ቁጥር - ዕጩ ተማሪው የሚገኝበት አድራሻ
- ለድርጅታችን የሚፃፉ መረጃዎች በሙሉ **"ለኢትዮጵያ ማሪታይም ትሬኒንግ ኢንስቲትዩት"** ተብለው መፃፍ ይኖርባቸዋል፡፡፡፡

**ደረጃ 3፡ የህክምና ምርመራ፡** የህክምና ምርመራው የሚደረገው በአዲስ አበባ ከተማ ብቻ ሲሆን የዋስትና ስምምነቶችን ከመፈረሙ በፊት ተቋሙ እውቅና በሰጠው ክሊኒክ ብቻ የሚደረግ ይሆናል

**ደረጃ 4፡** የቅበላ እና የዋስትና ስምምነቶች ከተፈረሙ በኂላ በባህርዳር መሠረታዊ የደህንነት ስልጠና የሚደረግ ነው

**ማሳሰቢያ፡** የቅበላ ስምምነቱ የፀና የሚሆነው ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ነው፡፡

**የኢ.ማ.ማ.ተ. አድራሻ**

አዲስ አበባ፣ አራዳ ክፍለ ከተማ፣ ቸርችል ጎዳና፣ ትራኮን ህንፃ 8ኛ ፎቅ

ስ.ቁ. 0930-00-0621

ኢ-ሜይል፡ MKidanie@emacrew.com